# ትምህርት 64

1. ሰው በዚህ ዓለም ያለው ሀብት ሁሉ ቢኖረው ገሃነም እሳት ከገባ በኋላ ሀብቱ ሊረዳው ይችላል?

ሀ- አይችልም።

2. ንብረቶቻችን ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ሊያድኑን ይችላሉ?

ሀ- አይችሉም።

3. ሀብታሙ ገበሬ ላይ ምን ደረሰበት?

ሀ- እግዚአብሔር እንዲሞት ጠራው።

4. ሰዎች ሁሉ የሚሞቱበትን ጊዜ የሚወስነው ማን ነው?

ሀ-እግዚአብሔር ብቻ ነው።

5. ሀብታሙ ገበሬ ብዙ ሀብት ነበረው፤ ለርሱ ያልነበረው ምን ነበር?

ሀ- የዘላለም ህይወት።

6. ከብዙ ሀብት የሚበልጥ ምንድን ነው?

ሀ- በእግዚአብሔር ማመንና የዘላለም ሕይወት ማግኘት።

7. ይህ የሀብታሙ ሰውና የአልዓዛር ታርክ እውነተኛ ታሪክ መሆኑን በምን እናውቃለን?

ሀ- ምክንያቱም እነዚህ ሁለት ሰዎች በእርግጥ በምድር ላይ ስለነበሩ ነው።

8. ሰው በሚሞትበት ጊዜ መንፈሱ የት ነው የሚሄደው ?

ሀ- ከእግዚአብሔር ጋር ለመሆን በቀጥታ ወደ መንግስተ ሰማይ ወይም የቅጣት ቦታ ወደ ሆነው ወደ ገሃም እሳት።

9. በመንግስተ ሰማይና በምድር መካከል የማቆያ ቦታ አለ?

ሀ- የለም።

10. በመጀመሪያ ሀብታሙ ሰው አብርሃምን የጠየቀው ምንድን ነው?

ሀ- አብርሃምን የጠየቀው አልዓዛር በጣቶቹ ጫፍ ውኃ ነክሮ ምላሱን እንዲያቀዘቅዝለት እንዲልክለት ነበር።

11. እግዚአብሔርን ለማመን የማይፈልጉ ሁሉ ከሞቱ በኋላ የሚሄዱት ወዴት ነው?

ሀ-ወደ ሲኦል ዘላለማዊ የቅጣት ስፍራ ወደሆነው ገሃም እሳት።

12. በእግዚአብሔር የሚያምኑ ሰዎች ሁሉ ሲሞቱ ወዴት ነው የሚሄዱት?

ሀ- ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር ወደ መንግስተ ሰማይ።

13. ወደ ቅጣቱ ቦታ የገባው ሰው ማምለጥ ይችላል?

ሀ- አይችልም።

14. ሀብታሙ ሰው ለአብርሃም ያቀረበው ሁለተኛ ጥያቄ ምን ነበር?

ሀ- በእሳት ባሕርና በዘላለማዊ የቅጣት ቦታ እንዳይሠቃዩ አልዓዛር ሄዶ ወንድሞቹን እንዲያስጠነቅቃቸው አብርሃም እንዲልከው።

15. አብርሃም የሀብታሙ ሰው ወንድሞች ማድረግ ያለባቸው ምንድን ነው አለ?

ሀ- እነርሱ ማድረግ ያለባቸው የእግዚኣብሔርን ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ ማንበብና መስማት ነው።

16. እኛ የእግዚአብሔርን ቃል የማንሰማና የማናምን ከሆነ ሊያድነን የሚችል ሌላ ነገር አለ?
ሀ- የለም።

- ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም የመጣው ለምንድን ነው አለ?

ማርቆስ 10፡45

45- ኢየሱስ እንዲህ አለ «የሰው ልጅ ሊያገለግልና ሕይወቱን ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ሊሰጥ መጣ እንጂ ሊገለገል አልመጣምና።»

- ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም የመጣው ወደ መንግስተ ሰማይ ለመግባት እርሱን እንድናገለግል ፈልጎ ነው?

- አይደለም።

- ኢየሱስ ምንም ነገር እንድንሰጠው አይጠይቀንም።
- ኢየሱስ ምንም ነገር እንድናደርግለት አይጠይቀንም።

- ኢየሱስ አምላክ ስለሆነ ምንም ነገር አያስፈልገውም።
- ኢየሱስ አምላክ ስለሆነ የሚያስፈልጉት ነገሮች ሁሉ አሉት።

- ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም የመጣው ሰዎች እንዲያገለግሉት አይደለም።

- ኢየሱስ ምን ላደርግ ወደዚህ ዓለም መጣሁ አለ?

- ሰዎችን ለማገልገልና ሕይወቱን ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ለመስጠት።

- ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ የኢያሪኮን ከተማ ለቅቀው ሲወጡ አንድ ዓይነ ስውር ለማኝ አጋጠማቸው።

ማርቆስ 10፡46

46- ከዚህ በኋላ ወደ ኢያሪኮ መጡ። ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ ከብዙ ሕዝብ ጋር ከኢያሪኮ ሲወጡ ዐይነ ስውሩ የጤሜዎስ ልጅ በርጤሜዎስ በመንገድ ዳር ተቀምጦ ይለምን ነበር።

- የዓይነ ስውሩ ለማኝ ስም ማን ነው?
- በርጠሜዎስ።

- የበርጠሜዎስ ዓይነ ስውርነት ስለ ሰዎች ምን ያሳስበናል?

- በርጤሜዎስ ዓይነ ስውር እንደ ሆነ ሁሉ ሰዎች እውር ሆነው መወለዳቸውን።

- ሰዎች ዓይነ ስውር ሆነው የተወለዱት እንዴት ነው?

- አዳምና ሄዋን በእግዚአብሔር ላይ ስላመፁ ዓየነ ስውሮች ሆኑ።

- አዳምና ሄዋን በእግዚአብሔር ላይ ስላመፁ ለእግዚአብሔር ነገር ዓየነ ስውሮች ሆኑ።

- ሰዎች ሁሉ ከአዳምና ሄዋን ስለተወለዱ ዓየነ ስውራን ሆነው ተወልደዋል።

- ሰዎች ሁሉ ከአዳምና ሄዋን ስለተወለዱ ለእግዚአብሔር እውነቶች ዓየነ ስውራን ሆነዋል።

- በርጤሜዎስ ማየት እንደማይችል ሁሉ እኛም የእግዚአብሔርን እውነቶች ማየት አንችልም።

- በርጤሜዎስ እንደገና ማየት እንዲችል በራሱ ማድረግ የሚችለው ነገር ነበር?

- አልነበረም።

- ሰዎች የእግዚአብሔርን እውነቶች ለማየት እንዲችሉ በራሳቸው ማድረግ የሚችሏቸው ነገሮች አሉ?

- የሉም።

- በርጤሜዎስ ማየት እንዲችል በራሱ ማድረግ የሚችለው ነገር እንደሌለ ሁሉ ሰዎች የእግዚአብሔርን እውነቶች ለማየት እንዲችሉ በራሳቸው ማድረግ የሚችሏቸው ነገሮች የሉም።

- የበርጤሜዎስ ዓይን እንዲያይ የማድረግ ችሎታ ያለው ማን ብቻ ነበር?

- ኢየሱስ።

- የሰዎችን ዓይን ማብራት የሚችል ማን ብቻ ነው?

- ኢየሱስ።

- የበርጤሜዎስን ዓይን ማብራት የቻለው ኢየሱስ ብቻ እንደሆነ ሁሉ የእግዚአብሔርን እውነቶች እንድናስተውልና እንድንረዳ ማድረግ የሚችለው ኢየሱስ ብቻ ነው።

-በርጠሜዎስ ኢየሱስን ምን ብሎ ጠራው?

## ማርቆስ 10፡47

47- እርሱም የናዝሬቱ ኢየሱስ መሆኑን በሰማ ጊዜ «የዳዊት ልጅ፤ ኢየሱስ ሆይ ማረኝ!» እያለ ይጮኽ ጀመር።

- በርጤሜዎስ ኢየሱስን ምን ብሎ ጠራው?
- የዳዊት ልጅ ብሎ ጠራው።

- በርጤሜዎስ ኢየሱስን የዳዊት ልጅ ብሎ የጠራው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም ኢየሱስ አዳኝ ነው ብሎ እግዚአብሔር ተስፋ የገባው የንጉስ ዳዊት ዘር ስለ ነበር።

- በርጠሜዎስ ራሱን መርዳት እንደማይችል አውቋል።

- በርጤሜዎስ እርሱን ሊረዳው የሚችለው ኢየሱስ ብቻ እንደሆነ አውቋል።

- በርጠሜዎስ ኢየሱስ ስለ ሠራቸው ተአምራት ሰምቶ ስለ ነበር ኢየሱስ እንዲረዳው ጮኸ።

- በርጤሜዎስ ኢየሱስ እንዲራራለት ጠየቀው።

- በርጠሜዎስ እርሱን ለመፈወስ የሚያበቃ ምንም መልካም ነገር እንደሌለው አውቋል።

- በርጠሜዎስ እርሱን ለመፈወስ የሚያስፈልገውን ነገር መክፈል እንደማይችል አውቋል።

- በርጤሜዎስ ኢየሱስ እርሱን ከፈወሰው ይህ የእግዚአብሔር ነጻ ስጦታ እንደሆነ አውቋል።

- እኛ ሁላችን በርጤሜዎስን እንመስላለን።

- ኃጢአት ስለ ሠራን ለፈውስ የሚያበቃን ምንም መልካም ነገር የለንም።

- የኃጢአት ቅጣት ሞት ስለሆነ ከዚህ ሞት ለመዳን የሚያስፈልገውን መክፈል አንችልም።

- ከተፈወስን ይህ የእግዚአብሔር ነፃ ስጦታ ብቻ ነው።

- በርጤሜዎስ ኢየሱስን የዳዊት ልጅ ሆይ ማረኝ ብሎ ስለ ጮኸ ሰዎች ምን አሉት?

ማርቆስ 10፡48

48- ብዙዎችም ዝም እንዲል ገሰፁት፤ እርሱ ግን «የዳዊት ልጅ ሆይ ማረኝ» እያለ የባሰ ጮኸ።

- ሰዎች በርጤሜዎስ ጸጥ እንዲል የገሰፁት ለምን ነበር?

- ሰዎች ኢየሱስ ደሃውን ዓይነ ስውር ለማኝ መርዳት እንደማይፈልግ አሰቡ።

- ኢየሱስ ደሃውን ዓይነ ስውር ለማኝ መርዳት አይፈልግም ያሉት እውነት ነውን?

-አይደለም።

- ኢየሱስ ደሃውን ዓይነ ስውር ለማኝ ለመርዳት ፈለጓል?
- አዎን።

- ኢየሱስ እያንዳንዱንና ሁሉንም ሰው መርዳት ይፈልጋል።

- ሰዎች ፀጥ እንዲል ቢገስፁትም በርጤሜዎስ ወደ ኢየሱስ መጮሁን ቀጠለ።

- በርጤሜዎስ ወደ ኢየሱስ መጮሁን በመቀጠሉ ኢየሱስ ጠራው።

ማርቆስ 10:49

49- ኢየሱስም ቆም ብሎ፥ «ጥሩት» አላቸው። እነርሱም ዓይነ ስውሩን፥ «አይዞህ ፤ተነሥ፤ ይጠራሃል» አሉት።

- በርጤሜዎስ ደሃና ዓይነ ስውር ቢሆንም እንኳን ኢየሱስ ስለ እርሱ ይገደዋል?

- አዎን።

- እግዚአብሔር ለሰዎች ሁሉ ይገደዋል?
- አዎን።

- ሁሉም ሰው ለእግዚአብሔር አስፈላጊ ነው።

- ረጅም ወይም አጭር ብንሆን ለእግዚአብሔር አስፈላጊዎች ነን።

- ጥቁር ወይም ነጭ ብንሆን ለእግዚአብሔር አስፈላጊዎች ነን።

- ሀብታም ወይም ድሃ ብንሆን ለእግዚአብሔር አስፈላጊዎች ነን።

- ጤናማ ወይም በሽተኛ ብንሆን ለእግዚአብሔር አስፈላጊዎች ነን።

- ብዙ ጥበብ ቢኖረንም ባይኖረንም ለእግዚአብሔር አስፈላጊዎች ነን።

- እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው በመውደድ ሰዎችን ሁሉ ለማዳን ይፈልጋል?

- አዎን።

- በርጤሜዎስ ኢየሱስ ሲጠራው ምን አደረገ?

ማርቆስ 10፥50-52

50- እርሱም ልብሱን ጥሎ ብድግ በማለት ተነሥቶ ወደ ኢየሱስ መጣ።

51- ኢየሱስም «ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋለህ»? አለው። ዓይነ ስውሩ፥ «መምህር ሆይ፤ እንዳይ እፈልጋለሁ» አለው።

52-ኢየሱስም «ሂድ እምነትህ አድኖሃል» አለው። ወዲያውም ዐይኑ በራለት፤ በመንገድም ኢየሱስን ተከትሎት ሄደ።

- በርጤሜዎስ ኢየሱስ ምን እንዲያደርግለት ፈለገ።

- በርጤሜዎስ ኢየሱስ ዓይኑን እንዲያበራለት ፈለገ።

- ኢየሱስ የበርጤሜዎስን ዓይን ማብራት ችሎ ነበር?
- አዎን።

- በርጤሜዎስ ኢየሱስ ዓይኑን ማብራት እንደሚችል አምኗል?
- አዎን።

- ኢየሱስ በርጤሜዎስ ማየት እንዲችል ማድረግ ችሎ ነበር?
- አዎን።

- ኢየሱስ "በርጤሜዎስ ስላመነ ማየት ችሏል" አለ።

- ኢየሱስ ወዲያውኑ የበርጤሜዎስን ዓይን አበራለት።

- የበርጤሜዎስ ዓይን እንዲያይ ማድረግ የቻለ ማን ብቻ ነበር?
- ኢየሱስ።

- የዐይነ ስውሩ ዓይን እንዲያይ ማድረግ የሚችለው ኢየሱስ ብቻ ነው።

- ዓይኖችን ሁሉ የፈጠረው እግዚአብሔር ስለሆነ ማየት እንድንችል ማድረግ የሚችለው እርሱ ብቻ ነው።

- ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ ወደ ኢየሩሳሌም በመቃረብ ላይ ሳሉ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ትእዛዝ ሰጣቸው።

ማርቆስ 11፡1-6

1-ወደ ኢየሩሳሌም በደብረ ዘይት ተራራ አጠገብ ወዳሉት ወደ ቤተፋጌና ወደ ቢታኒያ በቀረቡ ጊዜ፥ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን እንዲህ በማለት ላካቸው።

2-«በፊታችሁ ወዳለው መንደር ሂዱ፤ ሰው ተቀምጦበት የማያውቅ የአህያ ውርንጫ እዚያ ታስሮ ታገኛላችሁ፤ ፈትታችሁ አምጡት።

3-ማንም ‘ምን ማድረጋችሁ ነው?’ ቢላችሁ ‘ለጌታ ያስፈልገዋል፤ በቶሎም መልሶ ይልከዋል’ ብላችሁ ንገሩት።»

4-እነርሱም ሄዱ፤ በአንድ ቤት በራፍ ላይ እመንገድ ላይ የአህያ ውርንጫ ታስሮ አገኙት፤ ፈቱትም።

5-በዚያ ከቆሙት አንዳንድ ሰዎች «ውርንጫውን የምትፈቱት ለምንድን ነው?» አሏቸው።

6-ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስ ያላቸውን ለሰዎቹ በነገሯቸው ጊዜ ፈቀዱላቸው።

- ኢየሱስ ከደቀመዛሙርቱ ሁለቱ ምን እንዲያደርጉ አዘዛቸው?

- ወደሚቀጥለው መንደር ሄደው አህያ ፈትተው ወደ እርሱ እንዲያመጡ አዘዛቸው።

- ኢየሱስ አህያ እየሰረቀ ነበር?
- አልነበረም።

- ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱ አህያውን መልሰው እንደምያመጡ ለባለቤቶቹ እንዲነግሩአቸው ነገራቸው።

- ስለዚህ ሁለቱ ደቀመዛሙርት ወደ ሚቀጥለው መንደር ሄደው አህያውን አገኙ ወደ ኢየሱስም አመጡት።

- ደቀመዛሙርቱ አህያውን ይዘው ሲመለሱ ምን ሆነ?

ማርቆስ 11፥7-10

7- ውርንጫውንም ወደ ኢየሱስ አምጥተው ልብሳቸውን በጀርባው ላይ አደረጉ፤ እርሱም ተቀመጠበት።
8- ብዙ ሰዎች ልብሳቸውን በመንገድ ላይ አነጠፉ፤ ሌሎች ደግሞ ለምለም የዛፍ ቅርንጫፍ እየቆረጡ ያነጥፉ ነበር።
9- ከፊቱ የቀደሙትና ከኃላው የተከተሉትም በታላቅ ድምፅ እንዲህ ይሉ ነበር፤ «ሆሣዕና! በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው!
10- የምትመጣው የአባታችን የዳዊት መንግስት የተባረከች ናት! ሆሳዕና በአርያም!»።

- ኢየሱስ በውርንጭላዋ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ ሄደ።

- እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካኝነት በተናገረው መሰረት ኢየሱስ በአህያ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ገባ።

- ኢየሱስ በመጓዝ ላይ ሳለ ሰዎች አቀባበል አደረጉለት።

- ሰዎች ለኢየሱስ አቀባበል ያደረጉለትና ስለሚመጣው የዳዊት መንግስት የተናገሩት ለምን ነበር?

- ምክንያቱም ሕዝቡ ኢየሱስ የመጣው ከሮማውያን መንግስት አገዛዝ ነፃ ሊያወጣቸው እንደሆነ ስላሰቡ ነበር።

- ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም የሄደው ሕዝቡን ከሮማውያን አገዛዝ ነፃ ለማውጣት ነበር?

-አይደለም።

-ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም የሄደው ለምን ነበር?

- ኢየሱስ የሄደው ሕዝቡን ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ነፃ ለማውጣት ነበር።